# <u>አመርቂ ውጤት ለማግኘት አስቦ መንቀሳቀስ፡ ስለ ዴሞክራሲ ትግሉ አንዳንድ ጥያቄዎች፡፡</u>

<u>ብርሃኑ ነጋ</u>[1]

ከጥቂት ሳምንታት በፊት በሳን ሆዜ ከተማ ባደረግሁት ንግግር በኢትዮጵያ የሚካሄደው የዴሞክራሲ ትግል አመርቂ ውጤት እንዲያመጣ በመጀመሪያ በአካሄድ ደረጃ ይህ አሁን ፖለቲካችንን ቀፍድዶ ከያዘው የአሉባልታና የውሸት አባዜ መላቀቅ እንዳለበት ምሳሌ በመጥቀስ ለማሳሰብ መሞከሬ ይታወሳል፡፡ የዚህ አስፈላጊነት ደግሞ በትግሉ ወቅት በአልባሌ ወሬ የሚጠፋውን ጊዜ ከመቆጠብና ጊዜያችንንና ጉልበታችንን ዋናው የዴሞክራሲ ትግል ላይ በማትኮር የሚገኘው ትርፍ ላይ ያነጣጠረ ብቻ ሳይሆን በመሰረታዊ ደረጃ በእርግጥ የምንፈልገው የተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ለመፍጠር ከሆነ ይህን ስርአት ለመትከል የሚያስፈልገውን አነስተኛ ጨዋነትና ግብረገብነት ይህ ስርአት ይገባናል ብሎ ከሚታገለው ሃይል በተለይና ፖለቲካው ከሚመለከተው ማህበረሰብ በሙሉ የሚጠበቅ ሙሆኑን ለማሳሰብ ነበር፡፡

ያ ንግግር በተለይ በዝርዝር ለመመልከት የሞከረው ሁለተኛው ጉዳይ ስልጣንን በሚመለከት ያለንን አመለካከት ለማጥራት ይጠቅም እንደሆነ በሚል በስልጣን ዙሪያ ያነሳቸው ሀሳቦች ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር በአገራችን በአሁኑ ጊዜ የሚደረገው ትግል የፖለቲካ ስልጣኑን ማን ይያዘው የሚል ትግል ሳይሆን የፖለቲካ ስልጣን እንዴት ይያዛል? ከዚህጋር በተያያዘም በአገራችን እንደ ዜጎች መብታችን ተከብሮ፤ፍትህ አግኝተን ያለፍርሀት በነፃነት የምንኖረው እንዴት ነው? የሚለው መሰረታዊ የስርአት ለውጥ ጥያቄ መሆኑን ለመግለጽ ሞክሬአለሁ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም የዚህ አይነት ስርአት ለማምጣት የሚደረግ ትግል የጥቂት ሰዎች ትግል ሳይሆን የነጻነቱ ተጠቃሚ የሚሆነው ሁሉ አስተዋፅኦ የማድረግ የሞራል ግዴታ አለበት በማለት ተከራክሬአለሁ፡፡ በስልት ደረጃም ለእንዲህ አይነት እውነተኛ የስርአት ለውጥ የቆሙ ሀይሎች ሁሉ ሀይላቸውን አስተባብረው በጋራና በመከባበር መታገል እንዳለባቸው በአፅንኦት ተማፅኛለሁ፡፡

ከዚያ ውጪ ግን የዴሞክራሲ ትግላችን የታለመለትን ግብ በአጭር ጊዜ እንዲመታና በአገራችን በአምባገነን ስርአቶች በዜጎች ላይ ለዘመናት የደረሰው ለከት የሌለው አበሳና ሰቆቃ ለአንዴና ለሁሌም እንዲያበቃ ወይም ደግሞ በንግግሬ ላይ እንዳልኩት የመለስንና የጭፍሮቹን አገዛዝ በኢትዮጵያችን የመጨረሻው አምባገነናዊ አገዛዝ ለማድረግ የዴሞክራሲ ትግሉ ከአሁኑ መመለስ ያለባቸው ብዙ ጥያቄዎች እንዳሉና እነኝህን ጥያቄዎች በጥራት መመለስ ለትግሉ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን በመጠቆም እኔም እንደአንድ ዜጋ እነኝህን ጥያቄዎች ለመመለስ በመሞከር የክረምቱን ብርድ በመአከላዊ ፔንሲልቬንያ ተራሮች መሀል ተደብቄ አሳልፋለሁ ብዬ ለራሴ ቃል ገብቼ ነበር፡፡ በዚህ መሀል ነበር ዶ/ር ጥላሁን ከተደበቅሁበት ፈልጎ አውጥቶ ገና ጥያቄዎቹን በማብሰልሰል ላይ እያለሁ የካሊፎርንያ ፀሀይ ያስፈልግሃል ብሎ ነው መሰል የእኔን እምቢታ አልቀበልም ብሎ እዚህ ድረስ የጎተተኝ፡፡ እኔም እንደ ሌላው ጉዳዩ እንደሚመለከተው ኢትዮጵያዊ ለእነኝህ ጥያቄዎች ቢያንስ ለራሴ አመርቂ ነው የምለው መልስ እስከማገኝ ድረስ ከአሁን በሁዋላ እንደዚህ አይነት ከህዝብ ጋር የሚደረግ ውይይት ብዙ ትርፍ

---

[1] ጥር 9 ቀን፤ 2000 ዓ.ም. ሎስ አንጀለስ ከተማ

የለውም ብዬ ስለማስብ ይህ ንግግር እስከዚያ ድረስ የመጨረሻው ይሆናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ለማንኛውም ግን ዶ/ር ጥላሁንም ሆነ ሌሎች የቅንጅት የሎስ አንጀለስ ድጋፍ ሰጪ አባላት በዚህ በእናንተ ስብሰባ ላይ እንደ ግለሰብ ተገኝቼ ለጥያቄዎቻችሁ መልስ ለመስጠት እንኳዋን ባልችል እነኝህን ጥያቄዎች አብሬአችሁ እንድጠይቅ ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ እግዚአብሄር ያክብርልኝም እላለሁ፡፡ ከመንደርደሪያዬ ላይ ለመገመት እንደምትችሉት የዛሬ ንግግሬ ለምንም ጥያቄ መልስ ለመመለስ የታሰበ ሳይሆን ከትግሉ ጋር በተያያዘ መመለስ አለባቸው የሚባሉ ጥያቄዎችን ለማንሳት ነው፡፡ ይህ ለሁለት ቁምነገሮች ይጠቅማል ብዬ አምናለሁ፡፡ በመጀመሪያ ባለፈው ጊዜ እንዳልኩት የአገራችን ጉዳይ ይመለከተናል በምንል ሀይሎች መሀከል የሚደረገውን ውይይት ፍሬያማ ካልሆነ ተራ አሉባልታ አውጥቶ ትርፋማ በሆነና ትግላችንን በሚጠቅም መስመር ላይ እንዲያተኩር ይረዳዋል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ሁላችንም በእነኝህ ጥያቄዎች ዙሪያ ከስሜት የፀዳ አምክህኖታዊ ውይይት ከአሁኑ ከጀመርን ወደፊት የምንሄድበትን መንገድ አጥርተን በማየት ለዴሞክራሲ ትግሉ በሚሰለፉ ሀይሎች መሀከል በእውቀት ላይ የተመሰረተ የፀና የአላማ አንድነትን በመፍጠር፤ በቀላሉ የማይፍረከረክ የተባበረና ጠንካራ የዴሞክራሲ ሀይል ለመፍጠር ይረዳናል፡፡ እንዲህ አይነት ሀይል ደግሞ በትግሉ ወቅት ብቻ ሳይሆን ከትግሉም በሁዋላ ዴሞክራሲ በአገራችን ስር እንዲሰድ ለማድረግ ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

እነኝህን ጥያቄዎች በዝርዝር ከማንሳቴ በፊት ግን ጥያቄዎቹ የሚነሱበትን አስፈላጊ የአስተሳሰብ ምህዋር በሚመለከት አንድ ሁለት ሀሳቦች ላንሳ፡፡ እነኝህን ጥያቄዎች ለመመለስ ስንሞክር አላማችንን በመጀመሪያ ለራሳችን ግልፅ ማድረግ ይገባናል፡፡ ይህ ትግል የት ለመድረስ ነው? የሚለውን በጭንቅላታችን ስንመልስ ብቻ ነው ለጥያቄዎቹ የማስመሰያ ሳይሆን እውነተኛ መልስ መስጠት የምንችለው፡፡ መድረስ በምንፈልግበት ላይ ስምምነት ከሌለን ለሚነሱት ጥያቄዎች የምንሰጠውም መልስ የተለያየ ሊሆን መቻሉ ብቻ ሳይሆን የተመሳሰለ ሲመስል እንኳዋን ለተለያየ ውጤት እስከሆነ ድረስ አብሮ ለማታገል የሚችል የአመለካከት አንድነት አለ ማለት አይቻልም፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚፈጠር ጊዜያዊ አንድነት ደግሞ ዘላቂነት በሌለው የታክቲክ ፖለቲካ ውስጥ እስከ ወዲያኛው መዳከር ነው ትርፉ፡፡

ከዚህ አንፃር በመጀመሪያ ሁላችንም በእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአት መመስረት ላይ የማያወላውል ቁርጠኝነት ሊኖረን ይገባል፡፡ በትግሉ አካሄድ ላይ የሚነሱትን ጥያቄዎች የምንመልስበት መንፈስ ወደዚያ ስርአት ሊወስደን በመቻሉና ባለመቻሉ ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡ ምንም አይነት ጊዜያዊ ጥቅም ቢኖረው ይህንን ዋና ግባችንን የሚቀለብስ መልስ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፡፡ ሊመሰረት የሚገባው መንግስት በሌሎች ጥያቄዎች ላይ ተወደደም ተጠላም በህዝብ ነፃ ፍላጎት የተመሰረተ መሆኑ ላይ አጠቃላይ ስምምነት መኖር አለበት፡፡ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ማለት ግን ነፃ ምርጫ በማድረግ ላይ ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ ያሸነፈው ሀይል ተሸናፊውን የሚረግጥበት «የብዙሀን አምባገነንነት» አይደለም፡፡ በህዝብ ድምፅ ያሸነፈው መንግስት በምንም አይነት ሊረግጣቸው የማይችላቸውን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችም ያካተተ ነው፡፡ የመንግስት ስልጣን ከቁጥጥር እንዳይወጣ በተለያየ ተቋዋማዊና መዋቅራዊ ስርአቶች ለከት የሚያበጅ ስርአት ነው፡፡ ተሸናፊዎች ጊዜያቸውን ጠብቀው፤ አቋዋማቸውን አስተካክለው እንደገና ተወዳድረው ለማሸነፍ እድሉን የሚከፍትላቸው ስርአት ነው፡፡ አንዴ የተሳሳተ ሁሌም የሚሳሳት ከመሰረቱ ብልሹ ነው ብሎ የሚጥል አይደለም፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ

ያሉና የቆዩ ልዩነቶችን ዘላቂ መፍትሄ ለማበጀት፤ ተበደልን የሚሉ ማህበራዊ ሀይሎችን ለመስማትና ለችግራቸውም እውነተኛ መፍትሄ ለመፈለግ ክፍት የሆነ ስርአት ነው:: ይህን ለማድረግ እስከቻለ ድረስ ብቻ ነው የተረጋጋና የበለፀገ ህብረተሰብ ለመፍጠር የሚችለው::

እንዲህ አይነት ስርአት የመፍጠር አላማ ያነገበ ሀይል በጊዜው ያለውን ለከት የሌለው ስልጣን የሚፈልግ አምባገነን መንግስት ከመጣል ባሻገር መመልከት አለበት:: አምባገነናዊው ስርአትም ከወደቀ በሁዋላ የሚመሰረተው የመንግስት ስርአት የተረጋጋ ማህበረሰብ ለመፍጠር እንዲችል በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ልዩነቶች አጥርቶ መረዳት፤ እነኝህን ልዩነቶች በዴሞክራሲያዊው መርህ ላይ በመመስረት ከግጭት ውጪ የሚፈቱበትን መንገድ ማሰላሰል፤ ከቂምና ከጥላቻ የፀዳ ትንተና ማድረግ ብቻ ሳይሆን ይህንን ስሜት በተግባር ማሳየትና በዚያ የሞራል መርህ መንቀሳቀስ ይጠበቅብናል:: እንግዲህ በእነኝህ መሰረታዊ እምነቶች ላይ መለስተኛ ስምምነት ካለን፤ አሁን በፊታችን ላይ የተደቀኑ ዴሞክራሲያዊ ትግሉን በሚመለከቱ የሚነሱ ጥያቄዎችን በዝርዝር ማንሳት እንችላለን:: እነኝህን ጥያቄዎች በግል ማሰላሰል፤ በቡድን መወያየት ተወያይቶም አመርቂ መልስ መስጠት፤ የምንሄድበትን መንገድ አጥርቶ በማሳየት ወደምንፈልግበት ግብ በአጭር ጊዜ ያደርሰናል:: በዚህ አይነት አካሄድ የምንደርስበት ግብም ለዘላቂነት መረጋጋት ሊሰጠን የሚችል የፖለቲካ ማህበረሰብ የኀናፅፈናል:: ጥያቄዎቹም እነሆ፡

1. ከሰላማዊ ትግሉ ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጥያቄዎች

1) መለስ ባለ 8 ነጥቡ የቅንጅት ጥያቄዎች ላይ አልደራደርም ሲል ምን እየነገረን ነበር?

2) ኢህአዴግ የጥቅምት 22ቱን ጨካኝና አረመኔያዊ እርምጃ ሲወስድ እያስተላለፈ የነበረው መልእክት ምን ነበር? ጊዜያዊ የመደናበር እርምጃ ነው ወይንስ ከዚያ የጠለቀ መልእክት ነበረው?

3) እስር ቤት የነበረው የቅንጅት አመራር በተደጋጋሚ የዴሞክራሲ ሂደቱ ፈፅሙኑ ሀዲዱን እንዳይስት እንደገና ወደ ድርድር እንግባ ብሎ ሲጠይቅ ኢህአዴግም ሆነ በሱ የተላኩት «ዘላቂ መፍትሄ ለማግኘት አስታራቂ ነን» ባዮቹ ሽማግሌዎች ይህንን ማድረግ ያልቻሉት በእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ግንባታ ላይ ስላላቸው አቋዋም ምን ይነግረናል?

4) መጀመሪያ ላይ ተደረሰ ከተባለው ባለ ስምንት ነጥብ ስምምነትም ሆነ ከዚያ በሁዋላ ተጨምቆ በወጣው ባለ አምስት ነጥብ የማግባቢያ ሀሳብ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተስማምተዋል ተብሎ በዋናው ሽማግሌ ከተነገረ በሁዋላ ምንም ስምምነት እንዳልነበረ ሁሉ አቶ መለስ ሲክዱ ስለአቶ መለስም ሆነ ስለሽማግሌዎቹ የሞራል ምንነት ምን ይነግረናል?

5) ከዚያም በመለስ በመጨረሻ እንኩዋን ከእስር የመፈቻው ወረቀት እንዲፈረም የተደረገው ስምምነት ሁሉ ወዲያውኑ ፈፅሙኑ ሲጣስና ይባስ ብሎ ስምምነት ተብዬው ራሱ የኢህአዴግ የፕሮፓጋንዳ መሳሪያ ሲሆን ስለዚህ መንግስትም ሆነ በኢህአዴግ አጋፋሪነት ስለሚደረግ ሽምግልና ምን ይነግረናል? ከዚህ መንግስት ጋር የሚደረግ ማንኛውም ስምምነት እርግጠኛ ማሰሪያ ከሌለው በቀር ይህን መንግስት አምኖ ምን አይነት ድርድርስ ማድረግ ይቻላል?

6) እስረኞቹ ከተፈቱ በሁዋላም ሆነ ከዚያ በፊት የመለስ መንግስት ምንም አይነት ጠንካራና የህዝብ አመኔታ ያለው ሰላማዊና ህጋዊ ድርጅት እነዳይኖር እያደረጉ ያለው እንቅስቃሴ (የቅንጅትን ስም ለአየለ ጫሚሶ፤ የምርጫ ምልክቱን ለልደቱ፤በዚህ ሳምንት እንኩዋን የቅንጅትን አደራጆች አስረው ማንገላታታቸውን ይታዘቡዋል) ስለ ዘላቂ አላማቸው ምን ይነግረናል?

7) ከጥቅምት 22 እስከአሁን በኢህአዴግ መንግስት የሚሰራውን ሥራ ለተመለከተ ኢሕአዴግ ትክክለኛ ምርጫ አድርጎ ቢሸነፍ ስልጣኑን ለመልቀቅ ይፈቅዳል ተብሎ ይታሰባል ወይ? ትክክለኛ (ማለትም ነፃና ፍትሀዊ) ምርጫ ያደርጋል ተብሎስ ይታሰባል ወይ? (በቅርብ መለስ ስለ ኬንያ የሰጠውን ሃሳብ ላየ ፀቡ ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ጋር ብቻ ሳይሆን አፍሪካ ሁሉ እንደሱ እንዲሆን የሚፈልግ ተፅቢተኛ መሆኑን እያሳየን መሆኑን ከግምት በማስገባት፡፡)

8) ትክክለኛና ነፃ ምርጫ አይደረግም ተብሎ ከታሰበ፤ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ባጠቃላይና የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታው በተለይ ምን አቅጣጫ ይይዛል ተብሎ ይታሰባል?

9) እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ በአጭር ጊዜ አይኖርም ተብሎ ከታመነ ይህ ሁኔታ ተቀይሮ ዴሞክራሲያዊ ስርአት በሰላማዊ መንገድና በምርጫ እስከሚመጣ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል ተብሎ ይታሰባል? ምን ያህል ጊዜ ቢወስድስ ነው ይህ መንገድ ከጉዳቱ ጥቅሙ ይበልጣል ተብሎ እንደ ዋነኛ የትግል መሳሪያ ተይዞ ሊቀጥል የሚችለው?

10) ይህ የትግል ስልት በመጨረሻ ውጤት ያመጣል ተብሎ ቢታሰብ በምን ያህል የጊዜ ስሌት ቢመጣ ነው በእርግጥ ስልት ከመቀየር ይልቅ ይህንንው ስልት ውጤት እስከሚያፈራ ድረስ መጠበቅ የተሻለ አማራጭ ሆኖ የሚቀጥለው? (10 አመት? 20 አመት? 50 አመት? ከአስር አመት በታች ሊሆን እንደማይችል ኢህአዴግ በቅንጅት የቀረበለትን የ አምስት አመት የስርአት ለውጥ ሂደት አልቀበልም ብሎ ስለሆነ እዚህ ችግር ውስጥ የገባነው ቢያንስ 10 አመት መጠበቅ ዝቅተኛው ስሌት ነው ለማለት ነው፡፡)

11) ቅንጅት የሰላማዊ ትግል አማራጭን ሲወስድ ከግምት ያስገባቸው ስሌቶች ነበሩ፡፡ (ለምሳሌ ኢህአዴግ የህንን ሊቀበል ይችላል በውጭ ግፊትም ቢሆን፤ ይህ የትግል ስልት በአጭር ጊዜና በአነስተኛ ወጪ ውጤት ያስገኛል፤ ከዚህ ስልት ውጪ ያለው የአመፅ አማራጭ ውጤት ቢያስገኝ እንኩዋን ወጪው

ከፍተኛ ነው፤ ውጤቱም (ዴሞክራሲ ማምጣቱ) አጠራጣሪ ነው...ወዘተ.) እነኝህ ስሌቶች አሁንም ተቀባይነት አላቸው? ይህም ስሌት በመጠኑም ቢሆን ትክክለኛ ስለነበር ነው በምርጫ 97 ውጤት የተገኘ ው የሚባል ከሆነ አሁንም የዚያ አይነት ውጤት በዚያው ስልት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል ወይ?

12) ለሰው ህይወት ቅንጣት ታክል ክብር የሌለው፤ ለመግደል በፍፁም እማይሳሳ፤ የተፃፈ ሕግ ምንም ትርጉም የማይሰጠው፤ የፍትህ አካላቱን እጅግ ከማዋረዱ የተነሳ ምን እንደሚፈርዱ ከመንግስት እየተነገራቸው ብቻ ሳይሆን በተቻላቸው መጠን የመንግስት ባለስልጣኖች ገና የሚያስቡትን በመገመት እነሱን ለማስደሰት የሚፈልጉ ለሕግና ለሙያቸው ቅንጣት ተክል ክብር የሌላቸው ወገብ የለሽ ዳኞችን ሞልቶ እንደፈለገ በሚያሽከረክራቸው ሁኔታ ላይ ከዚህ መንግስት ጋር በሚደረግ ግጥሚያ ሰላማዊ ትግል እርግጥም ወጪው ትንሽ ነው ወይ? (በህይወት፤ በንብረት፤ በሰው ስነ ልቡና..ወዘተ.)

13) ሕግና የሚሰራ የፍትህ አካል በሌለበትስ ሰላማዊ ትግል ምን መልክ ይኖረዋል? አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት ምርጫ ብቻ ሳይሆን በሰላማዊ ትግል ማእቀፍ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም አይነት የሰላማዊ አመፅ እርምጃዎች (civil disobedience measures); ለምሳሌ ስራ ማቆም፤ ሰላማዊ ሰልፍ መውጣት፤ እቤት መዋል..ወዘተ. አሁን ባለው የኢህአዴግ ሁኔታ በአገር ውስጥ በመንግስት ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ማድረግ ይችላሉ ወይ?

14) አይደለም ለውጥ የሚያመጣ የሚችል ሰላማዊ ትግል፤ ነፃ የሆነ የሲቪክ ማህበረሰብ በአገሪቱ በፍፁም እንዳይኖርና በዚያ ክልል ስር ለመስራት የሚያስቡትን ፈፅሞ ለማሽማቀቅ የሰረቀውን ምርጫ ለምን ደፍራችሁ ታዘባችሁ ብሎ ዳንኤልና ነፃነትን አስሮ፤ በዚያ በካንጋሮ ፍርድ ቤት በሚያሳፍር ሁኔታ ካስፈረደባቸው በሁዋላ ፍርዳቸውን ጨርሰው እንኳዋን እንዳይወጡ እንደገና ይቅርታ ካልጠይቁ አልፈታም ብሎ እስከአሁን በእስር የሚያንገላታ ፍፁም ነውረኛ መንግስት ባለበት ለምን በሰላማዊ ትግል ለውጥ ይመጣል ብለን ለማመን ይቻለናል?

15) በተመሳሳይ መልኩ የሰዬን አፍ ለመዝጋትና «እርፎ እንዲቀመጥ» ለማድረግ የስዬ ወንድም በመሆኑ ብቻ አሰፋ አብረሀ ላይ በግፍ ያስፈረደበት ሳያንሰው የፍርዱን ጊዜ ከጨረሰም በሁዋላ በመያዢያነት (hostage) እስከአሁን በወህኒ ቤት የሚያማቅቅ አሸባሪ መንግስት ባለበት «ሰላማዊና ሕጋዊ» ትግል በእርግጥ ለውጥ የሚያመጣ ነው ወይንስ አንዳንዶች እንደሚሉት ማዘናጊያ?

2. ሥለ ትጥቅ ትግል የሚነሱ ጥያቄዎች:

ከላይ ያነሳሁዋቸው ጥያቄዎች እስከአሁን ቅንጅት እየተከተለ ያለውን የትግል ስልት ከገጠመው መንግስት መሰሪነት ጋር አብሮ ሲተያይ አይሰራም ተብሎ እንኳዋን ቢደመደም በቀጥታ የዚህ ተቃራኒ የሆነውና ጉልበትን በጉልበት ብቻ ነው መመከት የሚቻለው የሚለው አመለካከት በቀጥታ የሚመረጥ ነው ማለት አይደለም:: ይህም የትግል ስልት እንደሌላው አማራጭ ከላይ ካነሳናቸው የአመለካከት

መንደርደሪያችን አንፃር መፈተሽና ወደምንፈልገው ግብ በአጭር ጊዜና በአነስተኛ ወጪ ሊወስዱን መቻላቸውን መጠየቅ አለብን:: ከዚህ አንፃር የትጥቅ ትግል የተሻለ አማራጭ ነው የሚሉ ሰዎች የሚከተሉትንና ተመሳሳይ ጥያቄዎችን በአመርቂ ሁኔታ መመለስ ይጠበቅባቸዋል:

1) አሁን ባለው የአገራችንና የአካባቢያችን ሁኔታ (የመለስ መንግስት ካለው ወታደራዊ ሀይል፤ በጎረቤት ሀገሮች ካሉት የመንግስት አይነቶች፤የአሜሪካ መንግስት ለመለስ ከሚሰጠው ጊዜያዊ ድጋፍ፤..ወዘተ) በትጥቅ የሚደረግ ትግል በአጭር ጊዜ የመንግስት ለውጥ ያመጣል ተብሎ ይታሰባል ወይ? እንዲህ አይነት የትግል ስልት በአጭር ጊዜ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል የሚሉ ካሉ ሁኔታው ለዚያ አይነት ትግል ይመቻል የሚሉባቸው ምክንያቶች ምንድን ናቸው? እነኝህ ምክንያቶች አሳማኞች ናቸው ወይ?

2) የትጥቅ ትግልን እንደማሸነፊያ (ለመጨረሻው ድል) በመውሰድ ሳይሆን የዚህን መንግስት ትዕቢት ለማብረጃና ከዚያም ገፍቶ ወደ ድርድር ለማምጪያ ስፈልጋል ብለው ለሚያምኑ፤ በእርግጥ ይህ መንግስት በዚያ አይነት ግፊት ሊገብጥ የሚችል ነው ብለው ያስባሉ ወይ? ይህን እንዲያምኑ የሚያደርጋቸው ማስረጃ ምንድን ነው?

3) በእርግጥ በትጥቅ ትግል ይህን መንግስት ማንበርከክ ይቻላል ከተባለ፤ በምን ያህል ጊዜ ይህ ውጤት ሊገኝ ይችላል ተብሎ ይታሰባል? ይህስ የጊዜ ስሌት ከላይ በሰላማዊ ትግል ለውጥ ቢመጣ ይወስዳል ተብሎ ከተገመተው ጊዜ በምን ያህል ያንሳል? (ይህ እንግዲህ የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ በሰላማዊ ትግል ለውጥ ይመጣል ብለው የሚያምኑትን ከምር ከወሰድን ነው:: በሰላማዊ ትግል ለውጥ አይመጣም ብሎ ለደመደመ ይህ ጥያቄ ትርጉም አይኖረውም:: ያን ጊዜ ምርጫው አርፎ ያለነፃነት እየተገዙ መኖር ወይንም በዚህ የትግል ስልት መታገል ብቻ ነው የሚሆነው)

4) በትጥቅ ትግል ከሰላማዊ ትግል ባነሰ ጊዜ ለውጥ ይመጣል ተብሎ እንኳዋን ቢታሰብ የሚያስከፍለው ዋጋ ከባድ አይሆንም ወይ? ማህበረሰባችን እንዲህ አይነት ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ ነው ወይ? ይህ ዋጋ በሰላማዊ ትግል ወቅት (በተለይ ሰላማዊ አመፅ) ከሚከፈል ዋጋ ምን ያህል የከበረ ነው?

5) የሚከፈለው ዋጋ እንኳዋን ተከፍሎ መንግስት ለመቀየር ይቻላል ተብሎ ቢታሰብ፤ በጠመንጃ ሀይል ስልጣን ላይ የወጣ ሌላ ሀይል ልክ ኢህአዴግ እንዳደረገው ስልጣኑን ለከፈለው መስዋእትነት ቁዋሚ ክፍያ አድርጎ በመውሰድ ለሁሌም በጉልበት ስልጣን ላይ ለመቆየት አይሞክርም ብለን ለማመን እንችላለን ወይ? የዚህ አይነትስ እምነት መሰረት ምንድን ነው?

6) የትጥቅ ትግል በእርግጥም ውጤት ያስገኛል ተብሎ ከታሰበ፤ ላለፉት 15 አመታት ሲደረጉ የነበሩ የትጥቅ አመፆች ለምን ውጤት ማስገኘት አልቻሉም? ውጤት ያላስገኙት የትጥቅ ትግል በመሆናቸው ወይንም ይህ ስልት የማይሰራ በመሆኑ ነው ወይንስ በሌሎች ምክንያቶች? በሌሎች ምክንያቶች ከሆነ

(ሁሉም ታጣቂዎች የብሄርን ጉዳይ በዋናነት ያነገቡ መሆን፤ የተዳከመ አመራር ያላቸው ስለሆነ፤..ወዘተ) አሁን እነኝህን ድክመቶች አስወግዶ በተሻለ ሁኔታ ለመንቀሳቀስ ይቻላል ተብሎ ለምን ይታሰባል?

7) ማህበረሰባችን በምርጫ 97 ላይ በሰላማዊ መንገድ ለሚታገሉ ሀይሎች ከፍተኛ ድጋፍ እንደሰጠ ይታወቃል:: ከምርጫ 97 በሁዋላ በተፈጠረው አፈናና እስከአሁንም ኢህአዴግ እያሳየ ላለው ከፍተኛ ተፅቢትና የህዝብ ንቀት ህብረተሰቡ የትጥቅ ትግል አማራጭን የተሻለ አማራጭ አድርጎ የሚያይበትና የሚደግፍበት ሁኔታ ተፈጥሮአል ወይንም ይፈጥራል ተብሎ ይታሰባል?

8) የትጥቅ ትግል ብቸኛው አማራጭ ነው፤በአጭር ጊዜና በአነስተኛ ዋጋ ውጤት ሊያመጣ ይችላል ተብሎ ቢደመደምና ውጤቱንም ወደ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአት የሚወስድ ማድረግ ይቻላል ከተባለ፤ ይህን ለማድረግ የሚያስችለው ምን አይነት የጦር አደረጃጀት? ምን አይነት የጦርና የፖለቲካ አመራር፤ምን አይነት የፖለቲካ ስብስብ ነው? እንዲህ አይነት ስብስብ ለመፍጠር ይቻላል ተብሎ እንኳዋን ቢታሰብ፤ እንዲህ አይነቱ ስብስብ በሰላማዊ መንገድ ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ከሚታገሉ ሀይሎች ጋር የሚኖረው ግንኙነት ምንድን ነው የሚሆነው? የእንዲህ አይነቱ ሀይል የአጭርና የረጅም ጊዜ የፖለቲካ አላማዎች ምንድን ነው የሚሆኑት?

3. የትግል ስልትና ከኢህአዴግ ባሻገር በአገሪቱ የተረጋጋ ስርአት በመፍጠር ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች:

ከላይ የትጥቅ ትግልንም ሆነ ሰላማዊ ትግልን በመምረጥ በኩል የሚነሱት ጥያቄዎች ከጊዜና ከውጤታማነት አኩዋያ ሲመዘኑ የትኛው ይሻላል የሚለው አንዱን በመምረጥ ቢወሰን እንኩዋን በተመረጠው የትግል ስልት ተጠቅሞ የሚያሸንፈው ሀይል ልቡንና ሀይሉን በሙሉ ዴሞክራሲያዊ ስርአትን ለመገንባት ቢያውል እንኩዋን በአገሪቱ የረጅም ጊዜ ታሪክ የተፈጠሩ በተለይ ከዘውግ ጋር የተያያዙ ልዩነቶች ዘላቂ መልስ ካላገኙ የምንመኘውን የተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ለመፍጠር አይቻለንም:: እነኝህን ችግሮች ደግሞ ግድ የለም ከኢህአዴግ በሁዋላ እንመልሳቸዋለን ተብሎ የሚተዉ ሳይሆኑ ከአሁኑ በደንብ ታስቦባቸው ለመፍትሄ የሚሆኑ ሀሳቦች ከዴሞክራሲያዊ ሀይላት መፍለቅ አለባቸው:: ለዚህ እንዲረዳ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ስር ተሰልፈናል የምንል ሰዎች ከዚህ የሚከተሉትንና መሰል ጥያቄዎችን ማንሳትና መመለስ ይጠበቅብናል::

1) ከዘውግ (ብሄር) ጉዳይ ጋር በተያያዙ የሚነሱትን ጥያቄዎች በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ አገባብ ለመፍታት «ሁሉም ዜጋ እኩል ድምፅና በሕግ ፊትም እኩል ነው» የሚሉት መሰረታዊ መርሆዎች በተግባር መዋላቸው ብቻ ችግሩን በሙሉ ይፈታዋል ተብሎ ይታሰባል? የዘውግ ጥያቄ የሚያነሱት ሀይሎች ይህን ጥያቄ በማንሳታቸው ብቻ በግለሰብ ላይ ለሚመሰረት ዴሞክራሲ ጠንቅ ናቸው ተብሎ ይታሰባል?

2) በግለሰብ መብት ላይ የተመሰረተ (ግን የቡድን መብቶችን የሚያከብር) ዴሞክራሲያዊ ሀይል እነኝህ ሀይሎች አመለካከቱን እንዲጋሩትና የአጠቃላይ የዴሞክራሲ ትግሉ አካል ለማድረግ ምን አይነት እርምጃዎችን መውሰድ ይጠበቅበታል? በምን በምን ጥያቄዎች ላይ ነው መደራደርና መስማማት ይቻላል ተብሎ የሚታሰበው? ምን አይነት ጥያቄዎች ናቸው በምንም አይነት ለድርድር አይቀርቡም የሚባሉት?

3) ሕብረ ብሄራዊ ሀይሎች በመርህ ደረጃ በዘውግ ከተደራጁ ሀይሎች ጋር አብረው ለመታገል የሚያስችላቸው ሁኔታ አለ?

4) በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ተስማምቶ ግን ከነኛ በመለስ ባሉ ጉዳዮች ላይ ወደፊት ለህዝብ አቅርቦ በምርጫ ለማስወሰን የሚቻልበት አይነት መግባባት ቢፈጠር እነኝህን ሀይሎች በትግሉ ወቅት በጋራ በሚደረግ ትግልና በዚህም ሁኔታ በሚፈጠር የአብሮነት ስሜት በአንድ ላይ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት የሚያስችል የጋራ ራዕይ አብሮ ለማበልፀግ የሚቻልበት ሁኔታ ይፈጥር ይሆን? ወይንስ አንዳንዶች እንደሚሉት እንደዚህ አይነት ትብብር የዘውግ ሀይሎችን ጉልበትና ተቀባይነትን የሚያጎናፅፍ ለዘላቂ የዴሞክራሲ ትግሉ ግን ምንም ፋይዳ ያለው ጥቅም የማይሰጥ አካሄድ ነው?

5) የዘውግ ድርጅቶች በመሰረቱ ዴሞክራሲያዊ ሊሆኑ ይችላሉ? የራሱን በደል ለመቅረፍ ከመፈለግ ውጪ የሌላውን መብት የማይነካ ብሄረተኛነት ቢኖር በዘውግ በመደራጀቱ ብቻ ዴሞክራሲያዊ አይደለም የሚባልበት ሁኔታ ይኖራል?

6) በአንፃሩ «የብሄር መብቶችን የማያከብሩና በብሄረሰቦች በኩል የሚነሱ ታሪካዊ በደሎችን ለመስማት እንኳዋን ትዕግስት የሌላቸው ሰዎች ስለ ዴሞክራሲ ቢያወሩ የሚያምናቸው የለም» በሚል በተደጋጋሚ በግለሰብ መብት ዙሪያ የተሰባሰቡ ሀይሎች ላይ የሚሰነዘረው ክስ ምን ያህል እውነትነት አለው? እውነትነት ከሌለው ይህ አይነት ስሜት እንዳይኖርና ለትግሉ እንቅፋት እንዳይሆን ምን መደረግ አለበት?

7) አሁን አገራችን ባለችበት ሁኔታና የኢህአዴግ ትዕቢትና እምቢተኛነት በዚሁ ከቀጠለ፤ በትጥቅ ከተደራጁ ብሄረተኛ ድርጅቶች ጋር በትጥቅ ያልተደራጁ ለዴሞክራሲ የሚታገሉ ሀይሎች አብረው የተባበረ የፖለቲካ ትግል ለማድረግ የሚችሉበት ሁኔታ አለ? ወደፊትስ ይኖራል? ይህስ ለዘላቂው የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ የሚያግዘው ነገር አለ?

ለእነኝህ ሁሉ ጥያቄዎች ሁላችንም አንድ አይነት መልስ እንሰጣለን ማለት አይደለም። ልዩነቶች ሊኖሩ ይችላሉ፤ የሚጠበቁም ናቸው። ልዩነቶቹ ደግሞ አንዱ ወገን ምክንያታዊ ካለመሆኑ የተነሳ ብቻ አይደለም የሚፈጠሩት። በምክንያታዊ ሰዎችም መሀከል ልዩነት ሊኖር ይችላል። በጥሞና

ከተደማመጥንና በመጨረሻ ኢላማችን ላይ አንድ አይነት ግንዛቤ ካለን ግን ቀስ እያልን የሚነሱትን ልዩነቶች ማቀራረብ እንችላለን።

እነኝህ ጥያቄዎች ግን የእያንዳንዳችንን ምሁራዊ ጉጉት ለማስታገስ የቀረቡ ጥያቄዎች አይደሉም። ወደተግባር እንዲመሩን ተብለው የቀረቡ እንጂ። በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ስርአት ተመስርቶ ለማየት የምንፈልግ ሁሉ የእነኝህ ጥያቄዎች መልስ ተግባራዊ እንቅስቃሴያችንን ይመሩታል። በግልፅ አመለካከት ላይ የተገነባ የተግባር እንቅስቃሴ ደግሞ ውጤት የማስገኘት እድሉ ከፍተኛ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም። ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ የሚደረግ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ደግሞ በሁልቀሰብ ደረጃ የሚደረግ እንቅስቃሴ አይደለም። መደራጀት ይጠይቃል። ተደራጅቶ ለመንቀሳቀስ ደግሞ በሁሉም ጥያቄዎች ላይ ሁላችንም አንድ አይነት አመለካከት እንዲኖረን አይጠበቅም። በአንድ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ውስጥም ሆነንም በመሀላችን ልዩነት መኖሩ የሚያስደነግጠን ወይንም አብሮ የሚያታግለን አይደለም ብለን የምንተወው አይሆንም። ይህንን ደግሞ ለእናንተ መንገሩ ለቀባሪው ማርዳት ነው። ከትላንትና ወዲያ በዚሁ በሎስ አንጀለስ ከተማ የዴሞክራቲክ ፓርቲውን አርማ ይዘው ከሪፑብሊካኖች ጋር ለሚገጥማቸው የጥቅምት ፉክክር በሚያደርጉት የቅድመ ምርጫ ምርጫ ኦባማና ክሊንተን የጦፈ ክርክር ሲያደርጉ ተመልክታችሁዋል። ማንም አሸነፈ ማን ግን ጥቅምት ላይ አብረው ቆመው ባላንጣቸውን እንደሚታገሉ ጥርጥር የለም።

ከነኝህ ጥያቄዎች መልስ በመነሳትም ሆነ በሌላ ምክንያት የተለያየ ድርጅት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችም ግን የዴሞክራሲያዊ ስርአት የመገንባቱ ፍላጎት የምር ከሆነና ልዩነቶቹን ለህዝብ አቅርቦ በህዝብ ምርጫ ለመገዛት እስከተስማሙ ድረስ በዚህ ትግል ውስጥ አብሮ መስራት ብልህነት ነው። የኢህአዴግን መሪዎች ደግሞ እንቅልፍ የሚነሳቸው ትልቁ ነገር እንዲህ አይነት በዴሞክራሲያዊ መርህ ላይ የተመሰረተ አብሮ የመስራት ልምድ ሲዳብር መቻሉ ነው።

በመጨረሻም መልሼ መላልሼ ለማሳሰብ የምፈልገው ትግል በግለሰብ ደረጃ የሚደረግ አለመሆኑን ነው። መደራጀት አሁንም መደራጀት እጅግ አስፈላጊ ነው። ለዚህ ነው ዛሬ እዚህ የመጣችሁ ወገኖቼ በቅንጅት ድጋፍ ሰጪ ድርጅት ስር ያልተሰባሰባችሁ ካላችሁ እንድትቀላቀሉና የዴሞክራሲ ትግሉን በተግባር እንድትደግፉ የምማፀነው። አሁንም በእርግጠኛነት የምነግራችሁ ግን በምንም መንገድ ይምጣ ዴሞክራሲያዊ ስርአት በኢትዮጵያችን በፍፁም መምጣቱ አይቀርም። የፈለገውን ሀይል ይጠቀም፤ የፈለገውን ነውረኛ የብልጣ ብልጥ ስራ ይስራ ኢህአዴግ አሁን በያዘው መንገድ ለረጅም ጊዜ ሊቀጥል አይችልም። የኢትዮጵያ ህዝብ የዴሞክራሲ ፍላጎት ጂኒ ከጠርሙሱ ወጥቶአል፤ አይደለም የኢህአዴግ ተራ ብልጣብልጥነት ምንም አይነት ምድራዊ ሀይል መልሶ ወደ ጠረሙሱ አይከተውም።

አመሰግናለሁ